የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ- መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 29
ADDIS ABABA- 6th April, 2005

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፫/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈ ፀሚያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ገጽ ፫ሺ፹፪

## CONTENTS

**Proclamation No. 443/2005**

International Development Association Credit Agreement for Financing Post Secondary Education Project Ratification Proclamation ........ Page 3082

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፫/፲፱፻፺፯

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክት እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፳፯ሚሊዮን፬፻ሺህ ኤስ.ዲ.አር (ሃያ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፬ ቀን ፪ሺ፭ በዋሽንግተን ዲ.ሲ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፵፫/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 443/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE DEVELOPMENT CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS**, a Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association Provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 27,400,000 SDR (twenty seven million four hundred thousand SDR) for financing Post Secondary Education Project, was signed in Washington DC on January 4, 2005;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Development Credit Agreement at its session held on the 29th day of March, 2005:

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Post Secondary Education Project Ratification Proclamation No. 443/2005."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኀበር መካከል እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ ፬ ቀን ፪ሺ፭ በዋሽንግተን ዲ.ሲ የተፈረመው ቁጥር 3984ET የብድር ስምምነት ጸድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፯ሚሊዮን፬፻ሺህ ኤስ.ዲ.አር (ሃያ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Ratification of the Agreement

The Development Credit Agreement Number 3984ET signed in Addis Ababa on the 4th day of January 2005 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 27,400,000 SDR (twenty seven million four hundred thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the development Credit Agreement.

## 4. Effective Date

The Proclamation shall enter into force on the 6th day of April, 2005.

**Done at Addis Ababa, this 6th day of April, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ